# የአዋሽ ባንክ አክሲዮን ማህበር
# የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ

**መግቢያ፡-**

የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር መሥራቾች የባንክ ሥራ ስለመፍቀድና ስለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/1986 እና በ1952 በወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት ባንክ ለመመሥረት በመስማማት የባንኩን የመመሥረቻ ጽሑፍ በማዘጋጀትና በጊዜው የህግ ባለሙያዎች፣ የውልና ማስረጃ ምዝገባ መምሪያ ይባል በነበረው በማስመዝገብ ስራ ላይ እንዲውል ያደረጉ ቢሆንም፡-

- የአክሲዮን ማህበራት በሚመለከት በ1952 ዓ.ም. በወጣው የንግድ ህግ ላይ የተደነገጉት ሕጎች ተሽረው በ2013 ዓ.ም. በወጣው አዋጅ ቁጥር 1243/2013 (የኢፌዲሪ የንግድ ሕግ) በመተካቱ፤
- በአዲሱ የንግድ ሕግ መሠረት በአክሲዮን ማህበር የመመሥረቻ ጽሑፍ ውስጥ መካተት ያለባቸው ጉዳዮች እንደ አዲስ የተደነገገ በመሆናቸው፣
- የባንኩን የመመሥረቻ ጽሑፍ በማሻሻል ከአዲሱ የንግድ ሕግ ጋር ማጣጣም በማስፈለጉ፣

እኛ የአዋሽ ባንክ አክሲዮን ማህበር ባለአክሲዮኖች ህዳር 17 ቀን 2015 ዓ.ም. ባደረግነው የባለአክሲዮኖች 17ኛ አስቸኳይ ጉባዔ በቁጥር 200/4/87 ጥቅምት 21 ቀን 1987 ዓ.ም በውልና ማስረጃ ምዝገባ መምሪያ የተመዘገበውን የባንኩን የመመስረቻ ጽሑፍ በ2013 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 1243/2013 (የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሕግ) እና እና በባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 (በአዋጅ ቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለ) መሠረት በማሻሻል እንደሚከተለው አፅድቀናል።

## ምዕራፍ አንድ
## አክሲዮኖችና ባለአክሲዮኖች

### አንቀጽ 1: መሥራች አባላት

የባንኩ መሥራች አባላት በውልና ማስረጃ ምዝገባ መምሪያ በቁጥር 200/4/87 ጥቅምት 21 ቀን 1987 ዓ.ም በተመዘገበው የባንኩ የመመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 1 ስር ስማቸው የተዘረዘረው ናቸው።

### አንቀጽ 2: የባንኩ መጠሪያ ስም

የባንኩ መጠሪያ ስም አዋሽ ባንክ አክሲዮን ማኅበር ሆኗል።

Authentication & Service Branch 10 Office

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 10

## አንቀጽ 3: የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት

1. የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል።
2. ቅርንጫፎች እንደአስፈላጊነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ እና ከኢትዮጵያ ውጭ ሊቋቋሙ ይችላሉ።

## አንቀጽ 4: የባንኩ ዓላማዎችና ተግባራት

የባንኩ ዋና ዋና ዓላማዎችና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

1. ሁሉንም ዓይነት የንግድ ባንክ ሥራዎችን ማከናወን፣
2. ማንኛውንም ዓይነት ተቀማጭ ገንዘብ መቀበል፣
3. ብድሮችንና የኦቨርድራፍት አገልግሎቶችን መስጠት፣
4. በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ተከፋይ የሚሆኑ የውጭ ምንዛሪ ሠነዶችን፣ የቃል ኪዳንና የተስፋ ሠነዶችን እንዲሁም ሌሎች ሊዛወሩ የሚችሉ ገንዘብ ነክ ሠነዶችን ማውጣት፣ መቀበል፣ መግዛት፣ መሸጥ፣
5. በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ተከፋይ የሚሆኑ ቼኮችና የመንገደኛ ቼኮችን ማውጣት፣ መቀበልና መሸጥ፣
6. የውጭ ምንዛሪ መሸጥና መግዛት፣ በባንኮች መካከል በሚደረጉ የሥራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ፣
7. ካዝናዎችን ወይም የካዝናዎች ክፍሎችን ማከራየት፣
8. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባስቀመጠው/በሚያስቀምጠው ገደብ መሠረት በማናቸውም መንግሥታዊ እና/ወይም በግል ሥራዎች ውስጥ ኢንቨስት ማድረግ፣
9. በስቶክ ልውውጥ /ኤክስቼንጅ/ ሥራ መሣተፍ፣ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት በውክልና መሥራት፣
10. እንደሁኔታው የንግድ ሥራ ወኪል መሆን፣
11. አመቺ ሆኖ በተገኘ ሁኔታ ገንዘብን ኢንቨስት ማድረግ፣
12. ባለአደራ ሆኖ መሥራትና የንግድ ዋስትናን መስጠት፣
13. የንግድ ባንኮች ከሚሠሩዋቸው ሥራዎች ጋር ተጓዳኝ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ሁሉ መሥራት፣
14. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባስቀመጠው/በሚያስቀምጠው ገደብ መሠረት ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት መስጠት፣
15. በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት፣
16. የወኪል ባንኪንግ አገልግሎት የመስጠት፣
17. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚፈቅዳቸውን ቢተለምዶ እንደ ባንክ ሥራ የሚታወቁ ሌሎች ተግባራትን፣

## አንቀጽ 5: የባንኩ ካፒታል

1. የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ብር 11,989,236,000 ሆኗል።
2. የባንኩ የተከፈለ ካፒታል ብር 10,389,606,000 ሆኗል።

## አንቀጽ 6: አክሲዮኖች

1. የባንኩ የእያንዳንዱ አክሲዮን ዋጋ አንድ ሺህ ብር /ብር 1,000/ ነው።
2. የባንኩ አክሲዮኖች በባለአክሲዮኖች ስም የተመዘገቡ ተራ አክሲዮኖች እና የማይከፋፈሉ ናቸው።
3. ግለሰቦች/ድርጅቶች በጋራ አክሲዮን ለመግዛት ወይም የአክሲዮን ባለቤት መሆን ይችላሉ። ይህም በሚሆንበት ጊዜ ሁሉንም ግለሰቦች/ድርጅቶች በመወከል በሰብሰባዎች ላይ በቋሚነት ወይም በእያንዳንዱ የበጀት አመት የሚገኘውን ተወካይ መርጠው ይልካሉ።
4. አክሲዮኖችን ከተፃፈባቸው ዋጋ በታች ለማውጣት አይቻልም።

## አንቀጽ 7: የአክሲዮኖች የምስክር ወረቀት

1. እያንዳንዱ አክሲዮን የተፈረመ ሆኖ በንግድ ሕግ አንቀጽ 273 የተደነገገውን ዝርዝር መያዝ ይኖርበታል።
2. የአክሲዮን ባለቤትነት የምስክር ወረቀት የሚሰጠው በተከፈለው የአክሲዮን መጠን ብቻ ይሆናል።
3. ባንኩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከወረቀት አክሲዮኖች በተጨማሪ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ተፈጥረው በኤሌክትሮኒክስ የአክሲዮን ሒሳብ የሚያዙ ግዑዝ አልባ አክሲዮኖች ሊያወጣ ይችላል።
4. የባንኩ የአክሲዮኖች የምስክር ወረቀት በባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ተፈርሞ ይሰጣል።

## አንቀጽ 8: የባለአክሲዮኖች መዝገብ

1. በንግድ ሕግ አንቀጽ 274 የተደነገገውን ዝርዝር የያዘ የባለአክሲዮኖች መዝገብ በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ይኖራል።
2. የባለአክሲዮኖች መዝገብ በወረቀት ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊያዝ ይችላል።
3. ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ሥልጣን ያላቸው አካላት መዝገቡን ያለምንም ክፍያ ሊመለከቱት ይችላሉ።
4. ሌሎች ሰዎች መዝገቡን ለመመልከት፣ ግልባጭ ለመውሰድ ወይም የተወሰኑ ነጥቦችን ለመቅዳት የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚወስነውን ዋጋ ይከፍላሉ።

## አንቀጽ 9: አክሲዮኖች የማይከፋፈሉ ስለመሆናቸው

1. የባንኩ አክሲዮኖች የማይከፋፈሉ ናቸው፡፡
2. ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች የባንኩ አክሲዮን የጋራ ባለሀብት ከሆኑ የንግድ ሕግ አንቀጽ 270 ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 10: የባለአክሲዮኖች መብቶች

የባንኩ ባለአክሲዮኖች፡-

1. አዲስ በገንዘብ ተከፋይ የሚሆኑ አክሲዮኖችን ባንኩ ሲያወጣ በንግድ ሕግ አንቀጽ 448 መሠረት ባላቸው የአክሲዮን መጠን በቅድሚያ የመግዛት መብት፣
2. ከትርፍ ድርሻ ተከፋይ የመሆን መብት፣
3. በጉባኤዎች ላይ የመሳተፍ፣ ድምፅ የመስጠት፣ የመምረጥና የመመረጥ መብት፣ እንዲሁም
4. ሌሎች በሕግ የተሰጡ መብቶች ይኖራቸዋል፡፡

## አንቀጽ 11: መያዣነትና የአላባ ጥቅም

የባንኩ አክሲዮኖች በመያዣነት ወይም በአላባ ጥቅም ከተሰጡ የንግድ ሕግ አንቀጽ 271 ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 12: አክሲዮኖችን ስለማስተላለፍ

1. በሽያጭ የሚተላለፉትን አክሲዮኖች ነባር ባለአክሲዮኖች በቅድሚያ የመግዛት መብት አላቸው፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙን በሚመለከትም የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. አክሲዮኖችን የማስተላለፍ ተግባር በባለአክሲዮኖች መዝገብ ካልተመዘገበ በስተቀር ባንኩን በሚመለከት ረገድ ውጤት አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 13: የትርፍ ክፍፍል

1. በእያንዳንዱ የሂሣብ ዓመት መጨረሻ ከሚገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ ልዩ ልዩ ወጪዎች እና ወደ ተቀማጭ ሂሣብ የሚዛወረው ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ለባለአክሲዮኖች እንዲከፋፈል ጠቅላላው ጉባኤ ሊወስን ይችላል፡፡ ተቀማጭ ሂሳቡም ህጋዊ መጠባበቂያ እና በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የሚወሰኑ ሌሎች መጠባበቂያዎችን ይጨምራል፡፡
2. የትርፍ ክፍፍል ለባለአክሲዮኖች የሚፈፀመው ባለአክሲዮኖቹ በከፈሉት የአክሲዮን ዋጋ መጠን እና እና በአመቱ ውስጥ የነበረውን ቆይታ ታሳቢ በማድረግ ይሆናል፡፡
3. የትርፍ አከፋፈሉ ሁኔታ መቼና እንዴት መፈጸም እንዳለበት በዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል፡፡

Authentication & Service Branch Office
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
10

## አንቀጽ 14: ተጠያቂነት

ባለአክሲዮኖች ለባንኩ ግዴታዎች ተጠያቂ የሚሆኑት በየፉት የአክሲዮን ድርሻ መጠን ብቻ ነው።

## አንቀጽ 15: የባንኩ አስተዳደር አካላት

ባንኩ የሚከተሉት የአስተዳደር አካላት ይኖሩታል።

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ፣
2. ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣
3. የባንኩ ፀሐፊ፤
4. ኦዲተሮች፤

## ምዕራፍ ሁለት
## የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች

## አንቀጽ 16: አጠቃላይ ደንብ

የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የባንኩ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል ሆኖ፤ ውሳኔዎቹም በንግድ ሕግ አንቀጽ 391 መሠረት በሁሉም ባለአክሲዮኖች ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## አንቀጽ 17: የጠቅላላ ጉባዔ ዓይነቶች

ጠቅላላ ጉባዔዎች ባለአክሲዮኖቹን በሙሉ የሚይዙ ሆነው መደበኛ ወይም አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሊሆኑ ይችላሉ።

## አንቀጽ 18: የጉባዔ አጠራር

1. የጉባዔ አጠራር በመገናኛ ብዙሀን /ጋዜጣ፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን/ በሚወጣ ማስታወቂያ፣ በኤሌክትሮኒክ፤ በማህበራዊ ሚዲያ እና/ወይም ለአያንዳንዱ ባለአክሲዮን በሪኮማንደ በሚላክ ደብዳቤ ይሆናል።
2. የጥሪው ዝርዝር ይዘት በንግድ ሕግ አንቀጽ 371 እንደተመለከተው ይሆናል።

## አንቀጽ 19: የጉባዔው አጀንዳ

የጉባዔው አጀንዳ በንግድ ሕግ አንቀጽ 372 መሠረት ይዘጋጃል።

## አንቀጽ 20: የባለአክሲዮን እንደራሴ /ተወካይ/

1. ማንኛውም ባለአክሲዮን በባንኩ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የሚወክለውን አንድ እንደራሴ ለመሾም ይችላል።
2. እንደራሴው ባለአክሲዮን ላይሆን ይችላል።

3. ባለአክሲዮኑ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማህበር ከሆነ እንደራሴው ሥልጣን በተሰጠው የማህበሩ አመራር ይወከላል።
4. ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች በባንኩ ቦርድ ይወሰናሉ።

## አንቀጽ 21: የጉባዔው አመራር

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ፣ እርሱ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ በሹመት ቀደምትነት ያለው ዳይሬክተር፣ ቀደምትነት ያለው በማይኖርበት ጊዜ ደግሞ ጠቅላላ ጉባዔው የሚመርጠው ሰው የጠቅላላው ጉባዔ ሰብሳቢ ይሆናል።
2. ከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ ያላቸውና በጉባዔው ላይ የተገኙት አምስት ባለአክሲዮኖች በሚያደርጉት ስምምነት መሠረት ሁለቱ በድምፅ ቆጣሪነት ይሰየማሉ። ከፍተኛ እና ተመሳሳይ የአክሲዮን ይዞታ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ብዛት ከአምስት በላይ ከሆኑ ሁሉም አንድ ላይ ሆነው ድምፅ ቆጣሪዎቹን ይሰይማሉ።

## አንቀጽ 22: የጠቅላላ ጉባዔው ጸሐፊ

1. በንግድ ህጉ አንቀፅ 340 መሠረት የባንኩ ፀሐፊ ሆኖ የተሰየመ ሰው የጠቅላላው ጉባዔ ፀሐፊ ይሆናል።
2. የፀሐፊው ሥልጣንና ተግባራት በንግድ ህጉ አንቀፅ 341 እና በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 34 ላይ የተዘረዘሩት ናቸው።

## አንቀጽ 23: የድምጽ አሰጣጥ

1. እያንዳንዱ አክሲዮን አንድ ድምጽ ይኖረዋል።
2. የአንድ ባለአክሲዮን ወይም እንደራሴ ጥቅም ከባንኩ ጥቅም ጋር የሚጋጭበት ሁኔታ ሲያጋጥም ባለአክሲዮኑ ወይም እንደራሴው በድምጽ መስጠት መብቱ አይጠቀምም።
3. ዳይሬክተሮች የእነርሱን ተግባርና ኃላፊነት በሚመለከት ጉዳይ ላይ ድምጽ አይሰጡም።

## አንቀጽ 24: ጉባዔዎች

1. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው የሚካሄደው፣
   ሀ. የባንኩ የሂሳብ ዓመት ከተዘጋበት ቀን ጀምሮ ባለው 6 ወር ጊዜ ውስጥ፣
   ለ. በዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ መሠረት ሲጠራ ነው።
2. በሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በዲሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ መሠረት ይጠራል።

## አንቀጽ 25: የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣን እና ተግባራት

1. ጠቅላላ ጉባኤው በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SBB/71/2019 አንቀፅ 10.4 ላይ የተዘረዘሩትን ጨምሮ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፦
   ሀ. የባንኩን ዳይሬክተሮች ይሾማል፣ ይሽራል፣
   ለ. የባንኩን ኦዲተሮች ይሾማል፣ ይሽራል፣
   ሐ. የዳይሬክተሮችን አበልና የኦዲተሮችን የሥራ ዋጋ ይወስናል፣
   መ. የባንኩን የትርፍና ኪሳራ ሂሳብ እንደዚሁም የዲሬክተሮችንና የኦዲተሮችን ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፣
   ሠ. በትርፍ አከፋፍልና ካለፈው ዓመት የባንኩ ሂሳብ ጋር በተያያዘው ማናቸውም ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣
   ረ. የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ ያፀድቃል፤
   ሰ. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ ይመርጣል፣ ይሽራል፣ አበላቸውን ይወስናል፤
   ሸ. ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ተለይተው ያልተሰጡ ሌሎች ጉዳዮችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል።

## አንቀጽ 26: የመደበኛ ጠቅላላ ስብሰባ ምልዓተ ጉባኤና የድምጽ ብልጫ

1. ምልዓተ ጉባኤ የሚኖረው፣
   ሀ. የመጀመሪያ ጥሪ በሚደረግበት ጊዜ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ (ካፒታል) አንድ አራተኛ (1/4ኛ) የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎች ሲገኙ፣
   ለ. የሁለተኛ ጥሪ በሚደረግበት ጊዜ ድምፅ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች የሚወክሉት ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ግምት ውስጥ ሳይገባ በተገኙት አክሲዮኖች ውሳኔዎች ይተላለፋሉ።
2. ውሳኔዎች የሚያልፉት በድምጽ ብልጫ ነው። ድምጽ የሚሰጠው በወረቀት ከሆነ ያልተፃፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ከግምት ውስጥ አይገቡም።
3. በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመጠቀም የድምፅ ቆጠራ በማድረግ የጉባዔው ምልዓተ ጉባዔ መሟላቱን ማረጋገጥ እንዲሁም ለውሳኔ የሚሰጠውን ድምፅ መቁጠር ይቻላል።

## አንቀጽ 27: የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ. የባንኩን የመመሥረቻ ጽሑፍ የማሻሻል፤
ለ. የባንኩን ዋና ገንዘብ ማሳደግ ወይም መቀነስ፣
ሐ. ባንኩን የማፍረስ፣ የማዋሃድ፣ ወይም የመከፋፈል ውሳኔ መስጠት፣
መ. ሌሎች በሕግ ተለይተው የተሰጡትን ጉዳዮችን አይቶ ለመወሰን ይችላል።

## አንቀጽ 28: የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ምልዓተ ጉባዔና የድምጽ ብልጫ

1. ምልዓተ ጉባኤ የሚኖረው፣
   ሀ. የመጀመሪያው ጥሪ በሚደረግበት ጊዜ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች ውስጥ ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ (ካፒታል) አንድ ሦስተኛ (1/3ኛ) የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎች ሲገኙ፣
   ለ. የሁለተኛ ጥሪ በሚደረግበት ጊዜ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው ባለአክሲዮኖች ቢያንስ የማህበሩን ዋና ገንዘብ (ካፒታል) አንድ አራተኛ (1/4ኛ) የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎች ሲገኙ፣
   ሐ. የሦስተኛ ጥሪ በሚደረግበት ጊዜ ድምጽ መስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች የሚወክሉት ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ግምት ውስጥ ሳይገባ በተገኙት አክሲዮኖች ውሳኔዎች ይተላለፋሉ።
2. ውሳኔዎች የሚያልፉት ከተሰጠው ድምጽ ከሦስት እጅ በሁለቱ (2/3ኛ) ሲደገፉ ይሆናል። ድምጽ ያልሰጡትም ሆነ ያልተፃፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀት ግምት ውስጥ አይገቡም።
3. በንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ የተደነገገው ቢኖርም ባለአክሲዮኖች በነባር አክሲዮኖች ላይ የተፃፈውን ዋጋ በመጨመር የባንኩን ዋና ገንዘብ ማሳደግ የሚቻለው ባለአክሲዮኖች ራሳቸው ወይም እንደራሴዎቻቸው በሙሉ መገኘት በአንድ ድምጽ ሲደግፉ ነው።
4. ጉባዔው በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመጠቀም የድምፅ ቆጠራ በማድረግ ምልዓተ ጉባዔው መሟላቱን ማረጋገጥ እንዲሁም ለውሳኔ የሚሰጠውን ድምፅ መቁጠር ይችላል።

## ምዕራፍ ሦስት
## የሥራ አመራር

## አንቀጽ 29: የዳይሬክተሮች ቦርድ

1. የባንኩ ሥራ የሚመራው በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ በሚሾሙ አሥራ ሁለት /12/ አባላትን በሚይዝ የዳይሬክተሮች ቦርድ ይሆናል።
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ የሚካሄደው በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 14 እና 15፣ በንግድ ሕግ አንቀጽ 296 እና 298 እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ነው።
3. ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች የተደነገጉት ይሆናሉ።
4. የዳይዲሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ከወረቀት በሚዘጋጅ የምርጫ ካርድ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊካሄድ ይችላል፤ ለዳይሬክተሮች የሚሰጠው ድምፅ ቆጠራም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊካሄድ ይችላል።

5. የዳይሬክተሮች ቦርድ የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል። በሥራ ዘመናቸው መጨረሻ ላይ ዳይሬክተሮች እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ። የባንኩን ሥራ ቀጣይነት ለማረጋገጥ ከዳይሬክተሮቹ ቢያንስ አንድ ሦስተኛ /1/3/ የሥራ ዘመናቸውን ከፈጸሙ ዳይሬክተሮች መካከል ሊመረጡ ይችላሉ።
6. ዳይሬክተሮች ከመካከላቸው አንድ ሰብሳቢና አንድ ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ፣
7. የባንኩ ፀሐፊ የዳይሬክተሮች ቦርድ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል።
8. ዳይሬክተሮችን የመተካት ጉዳይ በንግድ ሕግ አንቀጽ 303 እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ይፈፀማል።

## አንቀጽ 30: የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣
   ሀ. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤዎችን ቃለ-ጉባዔዎች ይፈርማሉ፤
   ለ. የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣
   ሐ. የባንኩን የውስጥ ደንብ፣ ድርጅታዊ መዋቅር እና የደመወዝ መደብ /ስኬል/ ያጸድቃል፣
   መ. የባንኩን ዓመታዊ ረቂቅ በጀትና የሥራ ፕሮግራም ተመልክቶ ውሳኔ ይሰጣል፣
   ሠ. የባንኩን ፖሊሲዎች ያፀድቃል፤
   ረ. የባንኩን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ይሾማል፣ ይሽራል፣
   ሰ. የባንኩን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ደመወዝ ይወስናል፣
   ሸ. በዋና ሥራ አስፈፃሚው አቅራቢነት ለዋና ሥራ አስፈፃሚው ምክትል የሆኑ ኃላፊዎችን ይሾማል፣ ይሽራል፣
   ቀ. የቅርንጫፎች መቋቋምን ወይም መዘጋትን ሀሳብ ያፀድቃል፣
   በ. የባንኩ ሥራዎች በሕግ መሠረት መከናወናቸውን ያረጋግጣል፣
   ተ. የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈፃፀም መመሪያ በማዘጋጀት እንዲፀድቅ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፤
   ቸ. የባንኩ የውጭ ኦዲተሮች ሹመት እና የስራ ዋጋ እንዲፀድቅ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፤
   ኀ. ሌሎች በሕግና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።
2. አብዛኞዎቹ የቦርድ አባላትና የጉባኤው አስፈፃሚ አባላት በጋራ ሆነው የጠቅላላ ጉባኤዎች ስብሰባዎችንና ውሳኔዎችን ቃለ ጉባኤዎች ለሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት እያቀረቡ በባለአክሲዮኖች ስም ያስመዘግባሉ።
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ እንደአስፈላጊነቱ ሥልጣኑን በውክልና ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ የቦርድ አባላት ወይም ለዋና ሥራ አስፈፃሚው ሊሰጥ ይችላል።

## አንቀጽ 31: የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ በአካል በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ወይም በማናቸውም ሌላ ቦታ ወይም በኤሌክትሮኒክ ወይም በሌላ የመገናኛ ዘዴ ሊደረግ ይችላል።
2. ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ዳይሬክተሮች ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይኖራል።
3. ይህንን ጉዳይ በሚመለከት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ላይ አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በሌላ አባል ሊወከል ይችላል። ነገር ግን አንድ የቦርድ አባል በአንድ ስብሰባ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ የቦርድ አባላትን ወክሎ መሳተፍ አይችልም።
4. እያንዳንዱ ዳይሬክተር አንድ ድምጽ ብቻ ይኖረዋል።
5. ውሳኔዎች የሚሰጡት በድምጽ ብልጫ ይሆናል። የድምጽ አሰጣጡ እኩል በሚሆንበት ጊዜ የሰብሳቢው ድምጽ ወሳኝ ይሆናል።
6. የዳይሬክተሮች ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል። እንደ አስፈላጊነቱም ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።
7. የቦርዱ ውሳኔዎች በቃለ-ጉባዔ ተይዘው በስብሰባው ላይ በአካል ወይም በተወካይ በተገኙት የቦርድ አባላትና በማህበሩ ፀሐፊ ይፈረማል።
8. ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ይወስናል።

## አንቀጽ 32: የቦርድ ዳይሬክተሮች አበልና የሥራ ዋጋ

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለሚሰጡት አገልግሎት መጠኑ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት በጠቅላላ ጉባዔ ተወስኖ ከጠቅላላው ወጪ የሚታሰብ ዓመታዊ የሥራ ዋጋ ይከፈላቸዋል።

## አንቀጽ 33: ዋና ሥራ አስፈፃሚ

1. የባንኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሾማል፣
2. ዋና ሥራ አስፈፃሚው ከዲሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያና በመመሥረቻው ጽሑፍ እና አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት የባንኩን ሥራ ያካሂዳል።
3. የንዑስ አንቀጽ 2 ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።
   ሀ. ለዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ የሚያግዙ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ በሚፈልጉበት ጊዜም ያቀርባል፣
   ለ. የባንኩን ዓመታዊ ሪፖርት፣ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል፣ ሲጸድቁም በሥራ ላይ ያውላቸዋል፣

ሐ. ለዋና ሥራ አስፈፃሚው ምክትል የሚሆኑ ኃላፊዎችን መርጦ በዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲሾሙ ያቀርባል፣

መ. በማናቸውም የባንኩ ሥራ አመራር እና በፍርድ ቤት በሚታይ ማናቸውም ጉዳይ ባንኩን ይወክላል፣

ሠ. ቦርዱ በሚያወጣው ደንብና በሚያጸድቀው የደመወዝ መደብ /ስኬል/ መሠረት ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ከሥራ ያሰናበታል፣ ደመወዛቸውን፣ አበላቸውንና ሌሎች ጥቅሞችን ይወስናል፣

ረ. ባንኩን ወክሎ ገንዘብ ይበደራል፣

ሰ. የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣

ሸ. ክፍያዎችን ይፈጽማል፣ ይቀበላል፣

ቀ. ባንኩን ወክሎ ንብረት ይገዛል፣ ይሸጣል፣ ይከራያል፣ ያከራያል።

በ. የባንኩን ወኪሎች ይሾማል፣ ይሽራል፣ የሚከፈላቸውንም የሥራ ዋጋ ይወስናል፣

ተ. ቦርዱ በሚፈቅደው መሠረት ቅርንጫፍ ያቋቁማል፣ ይዘጋል፣

ቸ. የባንኩን ፀሐፊ ቅጥርና ስንብት ለቦርዱ አቅርቦ ያፀድቃል፤

ኀ. በሕግ የተሰጡትን ሃላፊነቶች እና በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

ነ. ከሥልጣኑ አስፈላጊ በሆነው መጠን ለባንኩ ሠራተኞች ወይም ለሌላ ሰው በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## አንቀጽ 34: የባንኩ ፀሐፊ

1. ባንኩ ተጠሪነቱ ለዋና ስራ አስፈፃሚው የሆነ ፀሐፊ የሚኖረው ሲሆን ቅጥርና ስንብቱም በዋና ስራ አስፈፀሚው ቀርቦ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚፀድቅ ይሆናል።
2. ፀሐፊው የሚከተሉት ተግባራትና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፦

ሀ. የማኅበሩን መረጃዎችና መዛግብት የማደራጀትና የመያዝ፤

ለ. ለሚመለከተው አካል ሪፖርቶችንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች በወቅቱ የመስጠት፤

ሐ. ለባለአክሲዮኖችና ለሶስተኛ ወገኖች መረጃ የመስጠት፤

መ. የባአክሲዮኖችን እና የቦርዱ አባላትን ስብሰባዎች የማዘጋጀት፤

ሠ. ቃለ ጉባኤዎችን ማዘጋጀትና አደራጅቶ የመያዝ፤

ረ. የተለያዩ የቦርድ ውሳኔዎችን ለማኔጅመንቱ በፅሑፍ ማሳወቅና ተፈፃሚነቱን መከታተል እና የክትትሉን ውጤት ለቦርዱ የማሳወቅ፣

ሰ. የጉባዔ ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (አቴንዳንስ) ማረጋገጥ፤

ሸ. ለስብሰባ የሚሆኑ አጀንዳዎችን ማዘጋጀትና ለቦርድ አባላቱ የመበተን፤

ቀ. ሪፖርቶችን፣ ቃለ-ጉባኤዎችን፣ ከብሔራዊ ባንክ የሚመጡ ደብዳቤዎችን እና ሌሎች ሰነዶች ሪከርድ አድርጎ የማስቀመጥ፤

በ. ሌሎች በቦርዱ እና በዋና ስራ አስፈፃሚው የሚሰጡ ተግባራትን የማከናወን።

## ምዕራፍ አራት
## ኦዲተሮች

### አንቀጽ 35: ኦዲተሮች

የባንኩ ኦዲተሮች በዳይሬክተሮች ቦርድ አቅራቢነት በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ይሾማሉ።

### አንቀጽ 36: የኦዲተሮች የአገልግሎት ዘመን

የባንኩ ኦዲተሮች የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት ነው።

### አንቀጽ 37: የኦዲተሮች ሥልጣንና ተግባር

የኦዲተሮች ሥልጣንና ተግባራት የሚከተሉት ይሆናሉ።

ሀ. የባንኩን መዛግብትና የዋስትና ሠነዶችን /ስኩሪትስ/ ይመረምራሉ፣

ለ. የባንኩን የንብረት ዝርዝር መዝገብ የሂሳብ ሚዛን እና የትርፍ ኪሳራ ሂሳብ ትክክለኛነት ያረጋግጣሉ፣

ሐ. የቦርድ ሪፖርት የባንኩን ትክክለኛ ገጽታ የሚያመለክት መሆኑን ያረጋግጣሉ፣

መ. በንግድ ሕግ አንቀጽ 349 መሠረት ለባንኩ ጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት ያቀርባሉ፣

ሠ. በሥራቸው ሂደት ውስጥ ያጋጠሙአቸውን ትክክለኛ ያልሆነ አሠራሮችን ለቦርድና ለጠቅላላው ጉባኤ በንግድ ሕግ አንቀጽ 350 መሠረት ያስታውቃሉ፣

ረ. የባንኩን የፋይናንስና የሥራ አመራር በሚመለከት በማንኛውም ጊዜ ድንገተኛ ምርመራ ያካሂዳሉ፣

ሰ. ሌሎች በሕግ እና በጉባዔው የሚሰጡ ሥራዎችን እና ሃላፊነቶችን ያከናውናሉ።

## ምዕራፍ አምስት
## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### አንቀጽ 38: ሂሳቦች

1. ባንኩ መዛግብትንና ሂሳቦችን በሕግና በንግድ ሥራ ተቀባይነት ባገኙ ደንቦችና የአሠራር ልምዶች መሠረት ይይዛል።
2. ዋና ሥራ አስፈፃሚው በዋናው መሥሪያ ቤትና በየቅርንጫፎቹ ሁሉ ደንበኛ መዛግብትና ሂሳቦች መያዛቸውን ያረጋግጣል።

## አንቀጽ 39: ሪፖርቶች

1. ባንኩ ለየበጀት ዓመቱ የሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ያዘጋጃል።
2. ባንኩ የትርፍና ኪሣራ መግለጫ ስለተከናወኑና ስለታቀዱ ሥራዎች አጫጭር ሪፖርቶች ያዘጋጃል።
3. የዳይሬክቶሮች ቦርድ በንግድ ሕግ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሠረት ሪፖርቶችን ያዘጋጃል፣ ለሚመለከታቸውም እንዲደርስ ያደርጋል።

## አንቀጽ 40: የሂሳብ ዓመት

የባንኩ የሂሳብ ዓመት እንደ አውሮፖ ዘመን አቆጣጠር ከጁላይ 1 ቀን እስከ ጁን 30 ቀን ድረስ ይሆናል።

## አንቀጽ 41: ስለባንኩ መፍረስ፣ መዋሃድና ሂሳብ ማጣራት

የባንኩ መፍረስ፣ መዋሃድ፣ መቀላቀል እና የሂሳብ ማጣራት ጉዳዮች በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 እና በንግድ ሕጉ መሠረት ይፈፀማል።

## አንቀጽ 42: ሕትመቶች

ማንኛውም ሕትመት፣ ምዝገባና በሕግ የሚፈለጉ የተለያዩ ሪፖርቶች በአዋጅ ቁጥር 592/2000 እና በ2013 ዓ.ም. በወጣው የንግድ ሕግ፣ መሠረት ይዘጋጃሉ።

## አንቀጽ 43: ባንኩ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

የባንኩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ይሆናል።

## አንቀጽ 44: ሌሎች የድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች

በተለያየ ጊዜ በባንኩ ድንገተኛ ጉባዔዎች የተወሰኑና በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች የማይቃረኑ ውሳኔዎች የፀኑ ናቸው።

## አንቀጽ 45: ማጽደቅ

እኛ የባንኩ ባለአክሲዮኖችም ሕዳር 17 ቀን 2015 ዓ.ም. ባደረግነው አስራ ሰባተኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ይህንን የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ አጽድቀናል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 10

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት
ቅ/10 ጽ/ቤት አ/አ
ፊርማው በጽ/ቤቱ ቀርበው ፊርመዋል::
ቁጥር 410/0006043/[illegible]/2015
21/06/2015

ጣሰው ተገኔ ደስታ
የሰነድ ማረጋገጥና መመዝገብ ባለሙያ IV
Tasew Tegene Desta
Document Authentication and Registration Expert IV

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት
...nts Authentication & ... Service Branch 10 Office

የሰነዶች ማረጋገጫና
ምዝገባ አገልግሎት
አዲስ አበባ (የቅርንጫፍ አስር ጽ/ቤት)

የገንዘቡ ልክ ብር 2046
በፊደል
ወይም ብር ____ የቴምብር ቀረጥ
የደረሰኝ ቁጥር 3903883
21 6 ቀን 20 15 ዓ.ም
የቴምብር ቀረጥ መቀበያ ኦፊሰር
ስም
ፊርማ